**ETHIOPIAN ASSOCIATION IN THE GREATER TORONTO AREA & SURROUNDING REGIONS**
**የኢትዮጵያውያን ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው**
2064 Danforth Ave., Toronto, Ontario, M4C 1J6
Tel: 416-694-1522 Fax: 416-694-8736, E-mail: office@ethiocommun.org
www.ethiocommun.org 1980-2006

# የዲሞክራሲ ሰማዕታትን ለማስታወስ የተዘጋጀ ሰላማዊ ሰልፍ። *A Demonstration of Remembrance*

**June 07, 2006**

## ጋዜጣዊ መግለጫ

የኢትዮጵያውያን ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው በወረሃ ግንቦት 1997 ዓ/ም በመላው ኢትዮጵያ የተካሄደውን ምርጫ አስመልክቶ ፍትህና ዲሞክራሲን ለማስፈን ሲታገሉ በወያኔ/ኢህአዲግ አስተዳደር የፀጥታ ኃይሎች በግፍና በአሰቃቂ ሁኔታ የተገደሉትን የኢትዮጵያ ብርቅዬ ልጆች ሙት ዓመት ለማስታወስ ቅዳሜ ጁን10, 2006 ዓ/ም ታላቅ ሰላማዊ ጠርቷል።

እኛም በውጭ ሃገር የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ለዲሞክራሲ ልዕልና ውድና መተኪያ የማይገኝለት ክቡር ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ ዕንቁ ወገኖቻችንን የምናስታውሰው ከልብ ሲሆን፤ ሃዘናችንም እጅግ ጥልቅና ቀጣይም ነው።

በቶሮንቶና አካባቢው የሚገኘው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ፤ ወያኔ/ኢህአዲግ የስልጣን መንበሩን በመሳርያ ሃይል ከተቆጣጠረ ጀምሮ በህዝባችን ላይ የሚፈጽመውን ጭካኔ የተሞላበት ዘግናኝ ድርጊትና ስልታዊ የስብዓዊ መብት ረገጣን ማውገዝና መቃወሙን ይቀጥላል። ይህ አምባገነን ስርዓት በተዋረድ ከላይ እስከ ታች በዘረጋው ኢዲሞክራሲያዊ መረብ ዙርያ ጥብቅና ታማኝ የፖለቲካ ደንገጡሮቹን በማሰማራት፤ የህዝቡን ድምፅ ለመንጠቅ ያደረገውን ተራ ማጭበርበር ያጋለጡ፤ የስርዓቱን አስተዳደራዊ ግድፈቶችና ስብዓዊ ነውሮቹን በገሃድ ያሳዩ፥ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች፥ ጋዜጠኞች፥ የስብዓዊ መብት ተማጓቾች ተማሪዎችና ንፁሃን ዜጎች በአሰቃቂ ሁኔታ በአልሞ ተኳሾች ጥይት ረግፈዋል። ሌሎችም በርካታ ወገኖች ህገወጥ በሆነ መልኩ ክብራቸው ተደፍሮ፤ ተደብድበውና ያለፍርድ ተይዘው እስከ አሁን በእስር ይማቅቃሉ

የወያኔ/ኢህአዲግ የ15 ዓመት አምባገነናዊ የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ አገራችን ኢትዮጵያን በቀላሉ የማይበርድ የፖለቲካ ፍላት ውስጥ አስገብቷታል። ለስርዓቱ ያደሩ ዳኞች የሀገሪቱ ህገ መንግስት የሚያዘውን የማይፈጽሙና የማይገዙለት ሲሆን፤ የፀጥታ አስከባሪ ኃይሎችም በፊናቸው ላዕላይ ህጉን የማያከብሩና ከዚህም ጋር ተያያዥነት ላላቸው አግባባዊ የዳኙነት ትዕዛዛት አሉታዊ አቋምን ይዘው ይታያሉ። በዚህም የተነሳ ኢትዮጵያ፤ ቀንደኛ አሳሪና ገዳይ ስርዓቶች በተሰለፉበት ጎራ ተፈርጃ፤ ልዩ የዕድገት ጉዞን በኋልዮሽ ተንፏቃቂ ስልት በተኩ የፖለቲካ ጭራቆች እየተመራች በማይነጥፍ ችግርና ሰቆቃ ውስጥ ገብታ ትታያለች።

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የማይጣጣምና የተዛባ ስርዓት ሰፍኗል። ፍትህ ለጊዜው በአገዛዙ መዳፍ ስር ወድቃ ህዝቡ መብቱን ተነፍጓል። በአንፃሩም የወያኔ/ኢህአዲግ አስተዳደር የሃገር ውስጥ ጉዳዮችንም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ግዴታዎችን መሸከም በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ተዘፍቆ ይዳክራል። ከዚህም የተነሳ ዛሬ ይህ አስተዳደር በድቡሽት ላይ እንደተሰራ ጎጆ፤ የእስትንፋስ እፍታና ኮሽታ ህልውናውን ስጋት ላይ ጥለውታል።
የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያዊንትን ጣርያ፥ ግድግዳና ምሰሶውን እንዲሁም ጠንካራ መሰረቱን አንፆ ያቆያቸው የወያኔ/ኢህአዲግ ከፋፋይ የፖለቲካ ርዕዮት ሳይሆን፤ ህዝባችን የፈጠረው የረጅም ዘመናት ባህላዊ ትስስር፥ የአንድነትና የጠንካራ ዜግነት ልዩ ዕምነታዊ ስሜት ነው።

የኢትዮጵያውያን ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው፤ ለኢትዮጵያውያን ለአፍቃሪ ኢትዮጵያና ለማንኛውም ሰላም ወዳድ ዜጋ ሁሉ በዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ እንዲሳተፉ ጥሪውን ሲያቀርብ፤ ሰልፉ የሚከተሉትን ዓበይት መርሆዎች ተመርኩዞና ግብ አድርጎ የተዘጋጀ መሆኑን ይገልፃል።

፩ በኢትዮጵያ ያለውን አሳሳቢ ጉዳይ አስመልክቶ ከሁሉም ሰላም ወዳድ ወገኖች ድጋፍን ለመሻት፤
፪ ኢፍትሃዊ ድርጊቶችን የፈፀሙ የወያኔ/ኢህአዲግ ባለስልጣናት ለፍርድ እንዲቀርቡ፤
፫ የታሰሩት ወገኖቻችን በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ፤
፬ የወያኔ/ኢህአዲግ የፀጥታ ኃይሎች ወደ ጦር ሰፈራቸው እንዲመለሱና፤
፭ የህግ የበላይነትና የዲሞክራሲ ልዕልና እንዲከበር፤

የሰልፉ መነሻ አደባብይ፥ ኮሌጅ ፓርክ /ጄራርድና ያንግ ጎዳና/ ኮሌጅ ስብዌይ አጠገብ ከቀኑ 12 Noon

ሰልፉ የሚካድበት ዕለት፥ ቅዳሜ ጁን 10 ቀን 2006 ዓ/ም
የእርስዎ በሰልፉ ላይ መገኘት የሰውን ሕይወት እንደማዳን ይቆጠራል።

የኢትዮጵያውያን ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው የዳይሬክተሮች ቦርድ

ዶ/ር ቡሻ ታአ፥ ፕሬዚደንት

## Press Release

The Ethiopian Community in Toronto has called a parade of remembrance to adore the courage of Ethiopians killed by the EPRDF security forces at the beginning of June 2005, while attempting to print democracy on the Ethiopian political page. We, Diaspora Ethiopians, take a serious note by remembering those jewels who made democracy their highest end – giving the most precious gift of no alternative.

**The Ethiopian Community in Toronto continues to condemn the blatant and systemic violation of human rights by the EPRDF regime. Some leaders of the political opposition, journalists, students and ordinary citizens were murdered in cold blood and others were violently beaten and put in prison for voicing against the post-election fraud and misgovernance. A decade and a half reign of absolute dictatorship has brought Ethiopia to its political boiling point. Neither the judiciary obeys the constitution that governs the behaviour of all nor do the security forces obey the judiciary. Thus, Ethiopia is a country of top jailers and most killers – led by political serpents – moving forward – using rare gear – a state of go nowhere.**

The present Ethiopia has become a nation of wrong equilibrium; the citizens have no rights and government has no proper duty. In fact, the government of Ethiopia is incapable of responding to domestic challenges or fulfilling its international responsibilities. As a result, the EPRDF has resembled a hut made of dry corn stack that requires only a gentle touch to collapse. What glued Ethiopia together is not so much political ideology but social biology – of nationalism - popular defiance to divisive governance.

The Ethiopian Association in GTA and the Surrounding Regions calls upon all peace- loving people to join the protest with the following objectives in mind:

- To draw the attention of all freedom loving people to the grave situations in Ethiopia.
- To gain support for bringing those who commit crime to justice.
- To immediately release political prisoners
- To return EPRDF's security forces to its barracks, and
- To respect the rule of law and the ideals of democracy

**Parade Starting Point: College Park (Gerrard & Yonge), College Subway Station**
**Time: 12 Noon Date: June 10, 2006**

Ethiopian Association in The Greater Toronto Area & Surrounding Regions Board of Directors
Busha Taa, Ph.D., President

በዕለቱ የመገናኛ ብዙሃን ዘጋቢዎች እንደሚሳተፉ ይጠበቃል።